የጉራጌ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅ/ጽ/ቤት

# የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት

እና

በጌታ ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት

# የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት መካከል የተገባ

# የ 2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል

ነሐሴ / 2013 ዓ.ም

ወልቂጤ

## 1. መግቢያ

የታክስ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች የመንግስት የወጪ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችል ገቢ ለመሰብሰብ፣ የገቢ ክፍፍል ለማድረግ፣የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለማስፈን፣ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት እና በማህበራዊ ግንኙነትና ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ጠቀሜታ የሌላቸውን ምርቶች አጠቃቀም ለመቆጣጠር ወይም ለመገደብ ነው። ታክስ ከእያንዳንዱ ግለሰብ የየዕለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ከነዋሪው ህብረተሰብ ተሰብስቦ ለራሱ መሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ማሟያ የሚውል የገንዘብ ምንጭ ነው።

መንግሥት ያለበትን ፊርጀ ብዙ ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልገውን በጀት ለመሸፈን ያስችለው ዘንድ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ገቢ የመሰብሰብ ሙሉ የሥልጣን ውክልና ከህዝቡ ተቀብሏል። በዚሁ መሠረት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ቀልጣፋና ውጤታማ የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር በመገንባት ለግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት መንግስትን ጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም ከማድረጉም በላይ ለሕዝቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በሚያደርገው ጥረት ትልቅ ሚና ይጫወታል። በሌላ በኩል የታክስ ስርዓትና አስተዳደር የሚገኝበት ሁኔታ የአንድ መንግስት የመልካም አስተዳደር ቁልፍ መለኪያ ሆኖ ይወሰዳል።

በገቢዎች ባለስልጣን አምስት የትኩረት መስኮች ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የአሰራር ልህቀትን ማረጋገጥ፣ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት ማምጣት፣ የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማምጣት ተቋማዊ የተለዩ ሲሆኑ እነዚህን የትኩረት መስኮች ለማሳካት የሚያስችሉ አስራ አምስት ስትራቴጂያዊ ግቦች ተለይተዋል ።

ከተለዩት አስራ አምስት ስትራቴጂያዊ ግቦች የሚጠበቀውን ዉጤት ለማረጋገጥ ተቋሙ የሚከተላቸዉ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓትን መገንባት፣ ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ፣ የዳበረ የሥራ ባህል መገንባት እና ስትራቴጂካዊ አጋርነትን ማጠናከር ናቸው ።

በ 2014 በጀት ዓመት 50.88 ሚሊየን/ ሃምሳ ነጥብ ስምንት/ ብር ለመሰብሰብ እቅድ ተይዟል።

## 2. የተቋሙ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች

## 2.1. ራዕይ

በ 2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ሙሉ በሙሉ ገቢ ተሰብስቦ ለልማት ውሎ ማየት

## 2.2. ተልዕኮ

ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባ ተቋም እና የሰዉ ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ የተጣጣመ ክልላዊና ዞናዊ የታክስ አስተዳዳር ሥርዓት በመገንባት፣ ፍትሀዊ፣ የላቀ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት አገልግሎት በመስጠት፤ ታክስ በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፤ የታክስ እና የገቢ ህግጋትን በማስከበር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ

## 2.3. እሴቶች

- አገልጋይነት
- አገልግሎትን በጊዜና በጥራት በመስጠት በልጦ መገኘት
- መስጠት
- ሙያና ክህሎትን ለተጨባጭ ውጤት መጠቀም /Professionalism/
- ታማኝነት
- ተጠያቂነት
- በትብብርና በውድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት

## 2.4 በ 2014 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ለመሰብሰብ የታቀደ ገቢ፦

- መደበኛ ገቢ ብር 45,863,172
- ማዘጋጃ ቤት ገቢ ብር 5,024,708
- ጠቅላላ ገቢ ድምር ብር 50,887,880

# 3. የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነዱ ማብራሪያ

## 3.1 የስምምነት ሠነዱ አስፈላጊነት

የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል መፈራረም እንደ አሠራር ሥርዓት ተድርጎ ሲሠራበት መቆየቱ ይታወቃል። በ 2014 በጀት ዓመትም ይህ የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሲዘጋጅ ተቋማዊ ጠቀሜታ እንደሚኖረው የሚታመን ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረው ቀርበዋል።

- ❖ የዞናችን የገቢ አቅም እና በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ እየተሰበሰበ የሚገኘውን ገቢ መጠን በመለየት የአካባቢው ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በወቅቱ በመሰብሰብ የውስጥ የፋይናንስ አቅማችንን በማጎልበት የዞኑን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት፣
- ❖ የጋራ ተቋማዊ ግብ በመጣል አሳታፊና ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት ለጋራ ውጤት ተናብቦ ለመስራት፣
- ❖ የየአከባቢው አስተዳደር አካላት የተቋሙን ግቦች እንዲያውቁ፣ የተገባውን ግዴታና የተሰጠውን ኃላፊነት በመገንዘብ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ለአፈፃፀሙ መሳካት አስፈላጊውን የሰው ሃይል፣ በጀት እና ሌሎች ግብአቶችን እንዲያሟሉ ለማድረግ፣
- ❖ በየደረጃው የሚገኙ የተቋሙ ሥራ አመራር አካላት፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ሠራተኞች የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ የሰጣቸውን ኃላፊነትና ያለባቸውን ተጠያቂነት ተገንዝበው ግዴታቸውን በዕቅድ፣ በዕውቀትና በአግባቡ ለመወጣት እንዲቻል ለማነሳሳትና ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው በመንቀሳቀስ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው።

## 3.2 የስምምነት ሰነዱ ዓላማ_

በበጀት ዓመቱ ሊተገበሩ የታቀዱ ተቋማዊ ስትራተጂያዊ ግቦችንና ከግቦቹ የሚጠበቁ ውጤቶችን በመለየት ዕቅድን በየደረጃው እስከ ፈፃሚ ባለሙያ ድረስ ቆጥሮ በመስጠትና ቆጥሮ በመረከብ መርህ መሠረት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ተግባዊ በማድረግ ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓት እና ተጠያቂነት በማስፈን ተቋሙን ውጤታማ ለማድረግ ነው።

## 3.3 የሰነዱ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነድ በጉራጌ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅ/ጽ/ቤት  የታክስ ትምህርት፣ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ እና በጌታ ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ ጋር በመፈራረም ተፈጻሚ ይደረጋል።

4. የጌታ ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት የ 2014 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድ

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1 ኛ ሩብ ዓመት** | **2 ኛ ሩብ ዓመት** | 3 ኛ ሩብ ዓመት | 4 ኛ ሩብ ዓመት |
| 1 | | | | | የማዘጋጃ ቤት ገቢ ጥናትና መመሪያ ዝግጅት ስርዓትን በማሻሻል ለገቢ አሰባሰብ የሕግ መሠረትና ውጤታማነትን ማሳደግ፡፡ | 1 | | | | | | | |
| 2 | | | የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል | 2 | የታክስ ትምህርት እና የህዝብ ግንኙነት የአሠራር ስርዓትን በማሻሰሻል ለገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሳደግ፡፡ | 0.5 | ያደገ ገቢ | በሚሊዮን ብር | **50.887** | **12.72** | **12.72** | **12.72** | **12.72** |
| 3 | | | | | የታክስ እና የአገልግሎት ቅሬታ አሠራር ስርዓትን በማዘመን (ፈጣንና ወቅታዊ ውሳኔ በመስጠት ገቢ እንዲሰበሰብ ማስቻል) | 0.5 | | | | | | | |
| 4 | ተገልጋይ | 10 | | | የማዘጋጃ ቤት ገቢ ጥናትና መመሪያ ዝግጅት አሳታፊነትነት በማረጋገጥ የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ ፡፡ | 2 | | | | | | | |
| 5 | | | የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ልህቀትን ማሻሻል | 8 | የታክስ ትምህርት እና ድጋፍ አሰጣጥ ውጤታማነትና ተደራሽነት በማስፋት የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ ፡፡ | 2 | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | የተገልጋይ እርካታ በመቶኛ | 90 | 90 | 90 | 90 | 90 |
| 6 | | | | | የታክስና የአገልግሎት ቅሬታ በወቅቱና ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ ፡፡ | 2 | | | | | | | |
| 7 | | | | | በባለስልጣኑ እና በሕብረተሰቡ መካከል መልካምና ጤናማ የሁለትዮሽ ግንኙነት በማስፈን አመኔታን ማሳደግ፡፡ | 2 | | ሕብረተሰቡ በታክስ ተቋሙ ላይ ያለው አመኔታ በመቶኛ | 90 | - | - | - | 90 |
| 8 | ፋይናንስ | 5 | የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | 5 | የሀብት አያያዝ፣ አጠቃቀምና ዉጤታማነት ማሳደግ፡፡ በበጀት አጠቃቀም ዙሪያ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡፡ | 5 | ዉጤታማ የሃብት አጠቃቀም | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የውስጥ አሰራር | 15 | የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ማስፈን | 15 | በከተማና ወረዳ ደረጃ የማዘጋጃ ቤት ገቢ ርዕስ የመጣኔ ተመን ጥናት ማካሄድ፡፡ | 5 | የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት | የተካሄደ ጥናት በቁጥር | 3 | መረጃ ማሰባሰብ | መረጃ ትንተናና የውሳኔ ሀሳብ | 3 የጥናት ሰነድ | - |
| 10 | | | | | የማዘጋጃ ቤት ገቢ ርዕስና መጣኔ ተመን መመሪያ ማዘጋጀት ፡፡ | 5 | | የተዘጋጀ መመሪያ በቁጥር | 3 | - | - | - | 3 መመሪያ ዝግጅት |
| 11 | | | | | የመጣኔ ተመን ጥናት እና መመሪያ ዝግጅት ድጋፍና ስምምነት መስጠት፡፡ | 2 | | ረቂቅ መመሪያ | 3 | - | መረጃ ትንተናና የውሳኔ ሀሳብ ክትትል | የጥናት ሰነድ | 3 መመሪያ ስምምነት |
| 12 | | | | | ተጠሪ ለሆኑ የአስተዳደር ዕርከን በተቋም ወይም በሥራ ዘርፍ ደረጃ የክትትልና ድጋፍ ስርዓትን ማሻሻል፡፡ የግምገማ እና ግብረ-መልስ ስርዓት መቅረፅ፡፡ | 2 | | የሕግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን ተፈጻሚ ያደረጉ የአስተዳደር እርከኖች በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 13 | | | | | ምርጥ ተሞክሮ መቀመር እና ማስፋፋት፡፡ እንዲሁም የልምድ ልውውጥ ለሚመጡ አካላት ልምድ ማካፈል፡፡ | 1 | | የተሞክሮ አይነት በቁጥር | 2 | | 1 | | **1** |
| 14 | የውስጥ አሰራር | 15 | የታክስ ህግ ተገዥነት አፈፃፀምን ማሻሻል | 15 | የታክስ ህጎች ግንዛቤ እና የተቋማዊ ገጽታ ግንባታ አፈጻጸም በማሻሻል ደረሰኝ ጠይቆ የሚገበያይ ህብረተሰብ ማሳደግ፡፡ | 2 | ያደገ የህግ ተገዢነት | ደረሰኝ ጠይቆ የሚገበያይ ገዥ ወይም ሸማች በመቶኛ | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| 15 | | | | | ለደረጃ “ሀ’’ እና “ለ’’ ግብር ከፋይ የክህሎት ሥልጠና ተደራሽነትን ማሳደግ፡፡ | 1 | | ተቀባይነት ያለው የሂሳብ መዝገብ የያዙ የደረጃ ‘ሀ’ እና ‘ለ’ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 80 | 80 | 80 | 80 | 80 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 16 | | | | | | 4 | | የክዕሎት ሥልጠና የተሰጣቸው የደረጃ ‘ሀ’ እና ‘ለ’ ግብር ከፋዮች በቁጥር | 13 | - | 13 | - | - |
| 17 | | | | | ለደረጃ “ሀ’’ እና “ለ’’ ግብር ከፋዮች በየወሩ የቤት ለቤት ድጋፍን ማጠናከር። | 4 | | የደረጃ ‘ሀ’ እና ‘ለ’ ግብር ከፋዮች ቁጥር | 13 | 13 | 13 | 13 | 13 |
| 18 | | | | | | 3 | | ግብር ከፋዮች ቁጥር | 653 | 164 | 163 | 163 | 163 |
| 19 | | | | | የፊት ለፊት ለግብር ከፋይ የሚሰጥ የታክስ ግንዛቤ እና የባህሪ ስልጠና ሽፋንን ማሳደግ። በፍቃደኝነት የሚከፈል የታክስ ድርሻን ማሳደግ። | 1 | | አዳዲስ ለተመዘገቡ ግብር ከፋዮች የፊት ለፊት የታክስ ግንዛቤ እና የባህሪ ስልጠና መስጠት (ለተመዘገቡት በሙሉ) በመቶኛ | 79 | 19 | 20 | 20 | 20 |
| 20 | | | | | የትምህርትና ድጋፍ ስትራቴጂ መተግበር፣ ትምህርቱ ያመጣውን ፋይዳ በመገምገም ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግ እንዲሁም ግብረ-መልስ መስጠት። | 1 | | ተጠሪ አስተዳደር ዕርከን በቁጥር | 1 | | | | 1 |
| 21 | | 17 | የህዝብ ግንኙነት እና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታ ማሻሻል | 17 | በታክስ ህግጋት እና ተቋማዊ ገጽታ ላይ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን እንዲሁም የህትመት ውጦቶችን አጠቃቀም ማሻሻልና ተደራሽነትን | 0.5 | የተገነባ ተቋማዊ ገጽታ | በሚኒሚዲያ የተላለፈ ትምህርት ፕሮግራም በቁጥር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 22 | | | | | | 1.5 | | በሶሻል ሚዲያ የተላለፈ መልዕክት በቁጥር | 104 | 26 | 26 | 26 | 26 |
| | | | | | | 0.5 | | በማይክራፎን የተላለፈ መልዕክት በቁጥር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| | | | | | | 1 | | በሞንታርቦ የተላለፈ መልዕክት በቁጥር | 5 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | | | 0.5 | | ብሮሸር ዝግጅት በዓይነት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1 ኛ ሩብ ዓመት** | **2 ኛ ሩብ ዓመት** | 3 ኛ ሩብ ዓመት | 4 ኛ ሩብ ዓመት |
| | | | | | ማሳደግ፡፡ | 1 | | ብሮሸር ስርጭት በቁጥር | 2000 | 500 | 500 | 500 | 500 |
| | | | | | | 1 | | ህብረተሰቡ አዘውትሮ በሚጠቀማቸው እቃዎች ላይ የተላለፈ መልዕክት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | | | 1 | | ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ስቲከር በቁጥር | 40 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 23 | | | | | | 0.5 | | የተዘጋጀ አርቲክል በቁጥር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 24 | | | | | | 0.5 | | ተዘጋጅቶ የተላለፈ የዜና ሽፋን በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | | | 0.5 | | ለማህበረሰቡ ተደራሽ የተደረገ አጫጭር መልዕክቶች በቁጥር | 1000 | 250 | 250 | 250 | 250 |
| | | | | | | 0.5 | | ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ባነር በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 25 | | | | | የገቢ ንቅናቄ በተለያዩ ፕሮግራሞች ማካሄድ፡፡ | 2 | | የተካሄደ ዞን አቀፍ የገቢ ንቅናቄ በቁጥር | 1 | - | - | 1 | - |
| 26 | | | | | በተለያዩ አደረጃጀቶች አማካኝነት የታክስ ህግጋት እና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታ ተደራሽነትን ማጠናከር፡፡ | 2 | | ለተለያዩ አደረጃጀቶች የተፈጠረ የግንዛቤ መድረክ በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 27 | | | | | በተቋሙ ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችና ቅሬታዎች እንዲሁም ምላሽ፣ ማብራሪያና ማስተካከያ የሚሹ ጉዳዮችን በየጊዜው በመከታተል ተገቢዉ ምላሽ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ማድረግ፣ | 1 | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 28 | | | | | በወቅታዊ አጀንዳዎች ላይ መግለጫ መስጠት፣ | 1 | | በመቶኛ | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1ኛ ሩብ ዓመት** | **2ኛ ሩብ ዓመት** | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 29 | | | | | የህዝብ ግንኙነትና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታ ሥራዎቹ ያመጡትን ለዉጥና ዉጤት በመገምገም ቀጣይነት ያለዉ የማሻሻያ እርምጃዎችን መዉሰድ። ግብረ-መልስ መስጠት። | 1 | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 30 | | | | | ከሚዲያ አካላት ጋር ውል መግባትና በተገባው ውል መሠረት ተፈጻሚነቱን መከታተል። | 1 | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 31 | **የውስጥ አሰራር** | 15 | የአሠራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል | 15 | በኦዲት ግኝትና በመደበኛ የታክስ ውሳኔ ላይ የቀረበ ቅሬታ የአሠራር ስርዓትን ማዘመን። | 6 | የላቀ የአሰራር ስርዓት | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ቅሬታ ምላሽ የተሰጣቸዉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 94 | 94 | 94 | 94 | 94 |
| 32 | | | | | በአገልግሎት አሰጣጥ የሚቀርብ ቅሬታና አለመግባባት የማጣራትና የአፈታት ሥርዓት ማሻሻል። | 4 | | በስታንዳርድ መሠረት የአገልግሎት ቅሬታ ምላሽ የተሰጣቸዉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 94 | 94 | 94 | 94 | 94 |
| 33 | | | | | በየደረጃው ምላሽ ያገኙ/ያላገኙ የታክስ እና የአገልግሎት ቅሬታ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ማሻሻል። | 3 | | የታክስ እና አገልግሎት ቅሬታ ውሳኔ አፈፃጸም ክትትል የተደረገባቸው ግብር ከፋይ በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 34 | | | | | የአገልግሎት አሰጣጥ የእርካታ ደረጃ ጥናት ሥርዓት ማሻሻል። | 2 | | የጥናት ሰነድ | 2 | - | 1 | - | 1 |
| 35 | **የውስጥ አሰራር** | 9 | የባለድርሻ አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | 3 | ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድና አፈጻጸም ውይይት፣የተለያዩ ስልጠና ስብሰባ ላይ ተሳትፎ በማድረግ አስተዋጽኦ ማበርከት። | 3 | የተፈጠረ ዉጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር፤ የተፈቱ ችግሮች | የተፈጠረ ውጤታማነት በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1ኛ ሩብ ዓመት** | **2ኛ ሩብ ዓመት** | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 36 | | | | | በኦዲት እና በሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ ግብረ መልስ አፈጻጸም ማሻሻል | 1 | | በኦዲት ግኝት የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 37 | | | ተቋማዊ የዉስጥ ስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል | 6 | መረጃን በአግባቡ ያለመያዝና ማዛበት የሚፈጸም የአሰራር ጥሰትን ማሻሻል። | 3 | የቀነሰ ተቋማዊ ስጋት | የስጋት ተጋላጭነት በቁጥር | 1 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 |
| 38 | | | | | የስነምግባር ግድፈት የመቀነስ አፈጻጸምን ማሻሻል። | 1 | | የቀነሰ የስነ ምግባር ግድፈት በመቶኛ | 1.73 | 1.73 | 1.73 | 1.73 | 1.73 |
| 39 | | | | | የስራ ተነሳሽነት ማሳደግ። የ 2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ከተጠሪ የአስተዳደር ዕርከን ጋር የዕቅድ ውል ስምምነት ማካሄድ። | 2 | | በየ 15 ቀኑ በዳይሬክቶሬት አደረጃጀት የተደረጉ ውይይቶች ብዛት | 26 | 6 | 7 | 6 | 7 |
| 40 | | | | | | 2 | | ከተቋም ኃላፊና ከፈፃሚዎችጋር የተደረገ የዕቅድ ውል ስምምነት ሰነድ በቁጥር | 1 | 1 | | | |
| 41 | መመልመልና ዕድገት | 13 | የሰው ሀብት የመፈጸም ብቃት ማሳደግ | 13 | ከታችኛው መዋቅር እስከ ዞን ማዕከል የተከናወኑ ተግባራት በየሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት በማጠናከር ለክልል ማቅረብ። | 4 | የረካ ሰራተኛ፣ ምርታማነቱ ያደገ ሰራተኛ | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 42 | | | | | የዕቅድ ውል ስምምነትና በአፈፃፀም ሪፖርት መነሻነት ለፈፃሚ የተሰጠ የቃል ወይም የጽሁፍ ግብረ መልስ | 2 | | በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |

| ተራቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ% | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1 ኛ ሩብ ዓመት** | **2 ኛ ሩብ ዓመት** | 3 ኛ ሩብ ዓመት | 4 ኛ ሩብ ዓመት |
| 43 | | | | | የሠራተኛውን እርካታና ምርታማነትን ለማሳደግ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ። ለፈጻሚዎችና ለዳይሬክቶሬቱ አስተባባሪዎች ሥልጣና መስጠት ወይም ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ። በተለይ በአሰራር ማንዋል፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በህዝብ ግንኙነት፣ በጥናትና መመሪያ ዝግጅት እና በስልጠና አሰጣጥ። | 3 | | በዙር | 2 | | 1 | 1 | |
| 44 | | | | | የምዘና እና የማበረታቻ ስርዓትን ማሻሻል። በየስድስት ወር የአፈፃፀም ምዘና በሥራ ዘርፍ፣ ዳይሬክቶሬት እና ፈጻሚ ደረጃ ማካሄድ። | 2 | | በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |
| | | 100 | 0 | 100 | 0 | 100 | | | | | | | |

**5.** የትግበራ ጊዜ

- ❖ ከሐምሌ 1/2013 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም

6. የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውሉን የተፈራረሙት አካላት

6.1. ይህን የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነድ የተፈራረሙት **የጉራጌ** ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ እና የጌታ ወረዳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ ናቸው።

6.2. **የጉራጌ** ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ

ስም ______________________________

ፊርማ__________________________ ማሕተም

ቀን __________________________

6.3. የጌታ ወረዳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ

ስም ________________________________

ፊርማ ____________________________________

ቀን ______________________________

6.4. የጌታ ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ

ስም ________________________________

ፊርማ ________________________________ ማሕተም

ቀን ______________________________